# ሕወሐት ከንቱ ማስፈራራት

***መንግስቱ ሙሴ***

**08/26/2016**

ሕወሐት ኢትዮጵያ ትበተናለች እኛ መኖራችን ተገቢ ነው እናም ዝቅ ብላችሁ የእኛን ፍላጎት እና አጀንዳ ብታስፈጽሙ ይሻላል የሚል ከግዜ ወደ ጊዜ የምንሰማው ማስፈራሪያ አለ። ብዙ ምሁራን ይህን አስተሳሰብ በነጠላው ይጋሩታል። ለምሳሌ አገሪቱ ከምትፈርስ ሰላማዊ የሆነ ሽግግር ያስፈልጋል ብለው ስለሚያስቡ አንድም የጥይት ጩኸት እንዲሰሙ አይፈልጉም። ሕወሐትም የምትፈልገው ይህንኑ ነው። እናም ነገር ጠንክሮ ሲገፋ ወዮ የለሁበትም ይህችን አገር ተጠንቅቄ የያዝኋት እኔ ነኝ። እኔ ከሌለሁ ደግሞ እንዴት አበላሽቼ እንደምሄድ አውቅበታለሁ ስትለን ቆይታለች። ከሁሉም በላይ የኦሮሞ ዜጎችን ለሌላው ማስፈራሪያ በማድረግ ስትቀሰቅስ እዚህ ደረሰች።

የአገሪቱን መፍረስ የሚፈሩ ዜጎች ከምንም በላይ አገር ይኑረን የሚለውን የጠላት ማስፈራሪያ ሲያራግቡ ኖረዋል። በእርግጥም ብዙ የሚያሰጋ ጉዳይ ነበረበት። ለፍርሀቱ አይነተኛ አመንክዮ የሚሰጠው ወያኔዋ ስብስብ አገር ሲፈርስ ወደትግራይ ትኮበልላለች የሚለው አስተሳሰብ ሲሆን። ይህ ደግሞ ነፍስ ዘርቶ የእውነታ ገጸባህርይ ይዞ የሚወጣው ከወያኔ ተፈጥሯዊ አስተሳሰብ እና ምኞት ጋር በሚቆራኝ ጥርጣሬ ነው። ጥርጣሬው እንዲህ ይነበባል። ላለፉት 25 አመታት እና ከዚያምበፊት በነበሩት ሕወሐት ገና በትግራይ ሜዳ እያለች በዘፈን፣ በሬዲዮ እና በፕሮፖጋንዳ ጽሁፎቻ ፍጹም ጸረ ኢትዮጵያ ሆና መታመኗ። ከዚያም እንደመንግስት ከተሰየመች በኋላ አገራዊ ፓርቲወችን እንዳይኖሩ ሌት ተቀን ሰርታ ስታፈርስ የዘር ድርጅቶችን ግን ማጠናከሯ። እርሷን ጨምሮ ከዚህችው ቡድን ጋር ተከትለው በድል አድራጊነት ወደስልጣን የመጡት ሀይሎች አሁንም በነጻአውጭነት መቀጠላቸው።

ከምርም ብዙ ዜጎች የሚጠይቁት ሕወሐት አገር አፍርሳ ለመሄድ እንጅ ዛሬ ደግሞ ከማን ነጻ ልትወጣ ነው ስሟን ጠብቃ የኖረች የሚል አግባብ ጥያቄ ብዙ ሰወች አላቸው። ወያኔም ችግር ቢፈጠር ወደ ትግራይ እመለሳለሁ የሚል እምነት ካላት በእውነት ትልቅ የድንቁርና አስተሳሰብ ለመሆኑ ለእኔ ጥርጥር የለውም። ምክንያቱ አንድ መንግስት ከማህል ሲፈርስ የትኛውም የሚያስጠጋው እንደሌለ መታወቅ ይኖርበታል። ሌላው ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ድል ስትሆን የመጀመሪያ ቀውስ በድርጅቷ በራሷ እና በሳተላይት ተከታዮቿ የመፈራረስ ነገር ይታያል። ወያኔ እንደድርጅት ታፈገፍጋለች የሚለው አስተሳሰብ ግንዛቤ እና ሎጅክ ይጎድለዋል።

ከዮጎዝላቪያ ትምህርት ስንወስድ

ዮጎዝላቪያ ስትፈጠር መጀመሪያ የአንደኛው የአለም ጦርነት ውጤት ናት። በአንደኛው የአለም ጦርነት ሰርቢያ ከተባበሩት የአውሮፓ ሀይሎች ጎን በመሆን የጀርመንን እና የኦቶማን ቱርክን ሀይል ተዋጋች። በጦርነቱ ማግስት ሶልቫኒያ፣ ኮሯት፣ ቦዝኒያ ከአውስትሮ ሀንጋሪያን ኢምፓየር ተለይተው ከሰርቢያ ኪንግደም ጋር ተዋሃዱ። በሁለተኛ የአለም ጦርነት እንደገና ዮጎዝላቪያ ፈረሰች። ለፍርሻዋ ምክንያትም ኩሯት የተባለችው ሬቡብሊክ ተገንጥላ ከጀርመን የናዚ ፓርቲ ጎን በመሰለፏ እና Part of the Third Reich የሶስተኛው ኢምፓየር አካል በመሆኗ ነበር። ከጦርነቱ ማግስት የአላያንሱ ጦር አሸንፎ፣ ከአላያንሱ ጎን የተዋጉት የዮጎዝላቪያ አርበኞችም በድል አድራጊነት በማርሻል ቲቶ መሪነት ሲመለሱዮጎዝላቪያ መልሳ ተዋሀደች።

በ 1990 የአሜሪካ ደህንነት አበክሮ እንደተነበየው በ 1992 ሶልቬኒያ ነጻ አገር መሆኗን ፓርላማዋ ወስኖ አስታወቀ። ተከታትሎ ኮሮሽያ እንዲሁ ነጻ አገር ነኝ በማለት ስታውጅ፤ በኮሮሽያ የሚኖሩ ሰርባውያን በሚሊሽያ ተደራጅተው ለነጻነታቸው መዋጋት ጀመሩ። ከዚያ በኋላ መንግስት አልባ እና የጋራ ስምምነት ጠፋ።

አገራችችን ከዚህ በብዙ ትለያለች

ወያኔወች እንደ የዘር ድርጅት እና ነጻ አውጭ ሆነው ለመቀጠል ምክንያታቸው ይህ የማስፈራራት ስራን ለመስራት። ብሎም ነገር ጠበቅ ካለ እኛ የማንገዛት ኢትዮጵያ መኖር የለባትም ከሚል ስሌት እንደሆነ ደጋግመው የሚናገሩት አስረጅ ነው። ግን ዛሬ የተፈጠረው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያመላክተው ተገላቢጦሹን ነው። የተበደሉ የእስልምና እምነት ወገኖቻችን ከቀሪው በደል ካንገፈገፈው ጎን መቆም። በሰሜን ጎጃሞች እና ጎንደሮች የወልቃይትን የማንነት ጥያቄ አንግበው መነሳት እና ትግሉ ቁርጠኛ የሆነ አንድ ምእራፍ ላይ መድረስ። በደቡብ እና ምስራቅ የኦሮሞ ወገኖቻችን በወያኔ ጥይት እየተደበደቡም ትግሉን መቀጠል እና አነሰም በዛ ከሰሜን ጋር ተየያዥ የሆነ ስነልቦና መኖሩ።

ሕወሐት በየትኛውም መልክ ልትፈርስ የምትችልበት አጋጣሚው ፈጦ የወጣ ገሀድ መሆኑ። ለዚህ ደግሞ ትግሉ በጠነከረ ቁጥር ወታደሮቿ ሊከዷት እንደሚችሉ ምልክቶች መኖራቸው። ሕዝብ የመታጠቅ አስፈላጊነት እና እየሞተም አልገዛም ብሎ ከሚገድለው መንግስት ፊት ለፊት ቆሞ ትግሉን መቀጠሉ እና ሌሎችም ሁኔታወች አገሪቱ ትፈርሳለች የሚለውን ስጋት እያቀጨጩት መሆኑ ነው። የልቅ ህዝብን ማደራጀት ማስታጠቅ፣ በትግሉ ሜዳ መሪወቹ እንዲወጡ ማገዙ የበለጠ የዚህችን ዘረኛ ቡድን እድሜ ሲያሳጥር። የህዝባችንን የጋራ ትግል እያጠናከረው ይሄዳል።

ኢትዮጵያ ዮጎዝላቪያ ወይንም እሩዋንዳ እና ቡሩንዲ አይደለችም። ታሪክ ያለው ሕዝብ አገር፣ ለዘመናት በክፉም በደግ አብሮ የኖረ ሕዝብ እየሞተም ዘር እና ጎራ ለይቶ አደጋ ባለማድረሱ። ጠላቴ ዘረኛው መንግስት ነው ብሎ መነቃነቁ ሁሉ ለስጋቶች ማፍረሻ እንደሆነ እናያለን። ሌላው ተቃዋሚ ድርጅቶች መተባበር መቻል አለባቸው። ይህ ደግሞ ጉልበትም ተስፋም ለእነርሱ የፖለቲካ በመጭዋ ኢትዮጵያ ይኖራቸው ዘንድ ይበጃል። ሕዝብንም በማገዝ ድልንም ያፋጥን ይችላል። አሁንም ተባበሩ አለያም ተሰባበሩ መፈክር ነው።

የትግራይ ምሁራን ዝምታ

ብዙ የምናውቃቸው፣ በወያኔ መዋቅር የሉም ተብሎ የሚገመቱ፣ እና በአገርም ሆነ በውጭ የሚኖሩ በስማቸው ግፍ ሲሰራ። አገር በወንበዴ መንግስት ስትቃጠ። አሰቃቂ ሁሉ ግፎች ሲፈጸሙ ዝምታን መርጠው መቀጠላቸው በእውነት አስተዛዛቢ እየሆነ መምጣቱን ግን መደበቅ አይቻልም። እንዴውም ጾያፍ የሆኑ ስድቦች እንኳን ሲወረወሩ በዚህ ሰአት እና ጊዜ ጾያፍነታቸውን ማመላከት አልታየባቸውም። እናም እስከመቸ እየጠበቁ ነው? ወይንስ ሳሞራ እንዳለው “የትግራይ ሕዝብ ማለት ሕወሐት፣ ሕወሐት ማለት የትግራይ ሕዝብ” የሚለውን እንደሚያጠናክር ማወቅ ያስፈልጋል። ትግራይ ያፈራቻቸው 16 ምሁራን ብቻ እንዳልሆኑ ደግሞ ሊታወቅ የገባዋል። እናም “ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ” ይባላል። ግዜው አሁን ነው በስማችሁ ሰው ሲገደል ዝምታ መጥፎ ምልክት ነው እላለሁ። ደግሞም ኢትዮጵያ ትቀጥላለች። ድሉም የህዝብ ነው።

ሕወሐት የጉም ሽንት ሆና እንደምትጠፋ ጥርጥር የለኝም። ምክንያቱም መንግስቱ 500 000 ጡር መርቶ መጨረሻ ብቻውን እንደሸሸ በእድሜአችን አይተናል። ያም እየተደገመ መሆኑን ዛሬም እያየን ነው። ለመሆኑ ግን ወያኔ የተባለች ድርጅት ብዙ ወርቃማ ግዜ አለፈባት« እራሷን አርማ በሰላም ለህዝብ የምትሰጠውን የህዝብ ስልጣን የሙጥን በማለት አልፎ ተርፎ ሽብር ውስጥ ገብታ ብዙ ህይወት በማጥፋቷ ግዜው መሸባት። የሌሎች አንባ ገነኖችን እጣ ፈንታ የምናይበት ግዜ እሩቅ አይድለም።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!

ሕዝብ ምንግዜም አቸናፊ ነው !!!!

http://www.ethiopanorama.com